ቁጥር OFAGF-03.24/5/5
ቀን 13/04/2015

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለኮምሽነር ጀነራል ደመላሽ ገ/ሚካኤል
የፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን ዋና ኮምሽነር

ለምክትል ኮምሽነር ጀነራል መስፍን አበበ
የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርስቲ ፕሬዘዳንት
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርስቲ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርስቲ የ2014 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 13 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 12 ገጽ የሂሳብ ሪፖርቶች በድምሩ 25 ገጽ የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከማክበር ሰላምታ ጋር

አበራ ታደሰ
የፌዴራል ም/ዋና ኦዲተር

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

Office of the Federal Auditor General

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት

የኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ/2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል። ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች

ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች(Basic of Audit Opinion)፣

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. ባልተሟላ ማስረጃ የተወራረደ የወጪ ሂሳብ፣

   የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 14 ተራ ቁጥር 4 መሠረት ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት ያዛል፡፡ የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች በንዑስ ቁጥር 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም ለአገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ሠነዶች በሙሉ ከክፍያው የወጪ ሠነድ ጋር መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ይገልጻል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ክፍያዎችን በመመሪያ መሰረት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

   የ20ኛ ዙር ምልምል ሰልጣኞች ከምልመላ ቦታ ወይም ከተመለመሉበት ክልል እና ዞን ለማስገባት እንዲሁም እነዚህን አዲስ ምልመል ሰልጣኞች ለመመልመል ከአዲስ አበባ ወደ ተለያዩ ክልሎች እና ዞኖች የተሰማሩ የተቋሙ አመራሮች እና አባሎች የተመደቡ መሆኑና በዚህም መሰረት ኢ/ር ታምራት ቢራ እና ዋ/ሳጅን ኅበዜ ቢራራ ቢጤ በተወከሉበት አካባቢ በስማቸው ብር 6,000,000.00 ከተሰጣቸው ቅድሚያ ክፍያ ውስጥ በድምር ብር 4,955,009.89 ያወራረዱ ቢሆንም፡-

   - ከቀረበው የሰልጣኞች ፊርማ ማስረጃ ላይ የአንድ ሰው ፊርማ ከተለያዩ ስሞች ላይ ተደጋጋሚ ተፈርሞ መገኘቱን፣
   - ለሰልጣኞች አበል ሲሰጥ አብዛኛው ፊርማ ተመሳሳይ በመሆኑ ብሩ ለሰልጣኞች መድረሱ አጠራጣሪ መሆኑን፣
   - የቀረበው የፊርማ ማስረጃ ምንም እንኳን አጠራጣሪ ቢሆንም ማስረጃው ላይ ምንም ያልፈረሙ ሰልጣኞች መኖራቸውና ነገር ግን አበሉ በስማቸው የተወራረደ መሆኑን፣

⁜ የውሎ አበል ተከፈሏል የተባሉት ሰልጣኞች ከክልል ወይም ከዞን ተመልምለው ሲመጡ ክልሉ/ዞኑ በቁጥር ስንት ሰልጣኝ ወደ ስልጠና ቦታ እንደላከና ማሰልጠኛ ቦታ ላይ ሲደርሱ ስንት ምልምሎች በትክክል ቦታው ላይ እንደደረሱ፣ እንዲሁም ሰልጣኞች መንገድ ላይ ለቆዩበት አበል ሲከፈል በምን አይነት የክፍያ ተመን እንደተከፈለ የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑን፣

በአጠቃላይ የቅደመ ክፍያ ሂሳብ ሲወራረድ ከላይ የተዘረዘሩት ማስረጃዎች ሳይሟሉ ክፍያ የተፈጸመና ሂሳቡ የተወራረደ በመሆኑ የክፍያውን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

2. <u>በተሰብሳቢ መመዝገብ ሲገባው በቀጥታ በወጪ የተመዘገበ በሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለ ወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብ እና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ አለበት በማለት ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም በፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 4"ለ" እና መ መሰረት የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መመዝገብ እንዳለበት እና ስራው በተጠናቀቀበት ደረጃ መጠን ብቻ በወጪነት መመዝገብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ለፎረንሲክ ምርመራና ላብራቶሪ ቢሮ፣ ለጥበቃ ማማ፣ የጥበቃ ቤቶች፣ አስፓልትና የአጥር ግንባታዎች ለማሰራት ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽንና ዲዛይን ሱፐርቪዥን ስራዎች ኮርፖሬሽን በብር 1,282,200,307.89 ውል የገባ ሲሆን በውሉ መሰረት ከአጠቃላይ የውል ዋጋ 10% የቅድመ ክፍያ ሲፈፅም በቀን 22/10/2014 ዓ.ም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 990769 በሂሳብ መደብ 6321 ብር 125,000,000.00 ምዝገባውን በቅድመ ክፍያ (4251) ሂሳብ መመዝገብና መክፈል ሲገባ በቀጥታ በወጪ በመመዝገቡ የወጪ ሂሳብ ሪፖርትን ያለአግባብ ከፍ ብሎ እንዲታይ ያደረገ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 2 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች እኛ አስተያየት የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ የሂሣብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበው ገቢ የተፈጸመው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (Emphasis matter)</u>፣

1. <u>ህጋዊ የክፍያ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ</u>፣

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ14 ንዑስ አንቀጽ 4እና7 መሠረት ለሚፈጸምባቸው ወጪዎች ተገቢውን የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃና ሥልጣን ባላቸው አካል መፈቀዱን ለማረጋገጥ የወጪ ሂሳቦች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፣ ዩኒቨርሲቲው ብር 116,700.00 ለተማሪዎች ምግብ የሚሆን አተር ክክ፣ ቀይ ጤፍ ግዥ የብቅል የህል ንግድ የጥቃቅን ኃ/የተ/የግል ማህበር ለተፈጸመ ክፍያ ህጋዊ ባልሆነ ደረሰኝ የተወራረደ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

2. <u>በተለያዩ ጊዜያት ለተሰጡ ስልጠናዎች ከመመሪያ ውጭ የተረደጉ የመስተንግዶ ወጪዎች</u>፣

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 25 ቀን 2009 ዓ.ም በበጀት ላይ የወጪ ቅነሳ መሰረት በተራ ቁጥር 7 የመስተንግዶ ወጪን በተመለከተ በየመ/ቤቱ ለሚደረጉ የመስተንግዶ ወጪዎች በአግባቡ በመፈተሽ አላስፈላጊ ወጪዎችን መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በየመ/ቤቱ ለሚደረጉ ስብሰባዎች፣ ወርክሾፖች እና ሴሚናሮች እንደ ሻይ፣ ቡና እና ውሃ ከመሳሰሉት ወጪዎች በስተቀር ሌላ ግብዣ ማድረግ እንደማይቻል ገልጿል፡፡ በተጨማሪም ከባለድርሻ አካላት ጋር ለሚካሄዱ ስብሰባዎች እና ክብረ ባዕሎች ለተሳታፊዎች የሚሰጡ ቦርሳ፣ ቲሸርት፣ ካኒቴራ፣ ኮፍያ፣ ሻርፕ እና የተለያዩ የሀገር ባህል ልብሶች መግዛት አይቻልም፡፡ በተቻለ መጠን ስብሰባዎች በየተቋማቱ መሰብሰቢያ አዳራሾች በማካሄድ ለሆቴሎች

የሚወጣውን ወጪ ማስቀረት ይገባል ይላል፡፡ በዚህም መሰረት መ/ቤቱ ከላይ የተገለጸውን መመሪያ ተከትሎ እንደሚሰራ ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣ ዩኒቨርሲቲው በግንቦት ወር ለሚካሄደው አገር አቀፍ ሲምፖዚየም የሚሆን 175 የሰነድ መያዣ ቦርሳ በቀን 25/09/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0402472 በድምር ብር 398,124.83 ያለአግባብ ከወጪ ቅነሳ መመሪያ ውጭ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ፣</u>

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል አንድ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ዕቃው ወደ መ/ቤቱ ዕቃ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረቡ ማረጋገጥ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ በዩኒቨርስቲው በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ የወጪ ሂሳቦች በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

በዩኒቨርስቲው በሂሳብ መደብ 6217 የነዳጅና ቀባት ክፍያ ከናሽናል ኦይል ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በተለያየ ወጪ ማስመስከርያ በጠቅላላ ድምር 10,706,509.24 ብር ለነዳጅ ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም ነዳጁ ወደ ንብረት ክፍል መግባቱን የሚያረጋግጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑንበኦዲት ተረጋግጧል፡፡

4. <u>በመድሃኒት ገቢ ደረሰኝ ገቢ መሆን ሲገባው በዕቃ ገቢ ደረሰኝ ገቢ የተደረገ የመድኃኒት ግዥዎች፣</u>

የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 2006 ዓ.ም ባወጣው የፌደራል ሆስፒታሎች የመዳሃኒት አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 001/2006 ተራ ቁጥር 6.2 ማንኛውም መድኃኒት ወደ ሆስፒታል ገቢ ሲደረግ የመድኃኒቱን የምርት መለያ ኮድ እና አገልግሎት መግለጫ፣ መጠን፣ መለኪያ፣ የነጠላ ዋጋ፣ የዉስጥ መለያ ኮድ እና አገልግሎት ዘመኑን በሚገልጽ ለዚሁ አላማ ተብሎ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚታተም የመድኃኒት የገቢ ደረሰኝ መሰረት በበጀት ምንጫቸው ተለይተው መሆን አለበት ይላል፡፡ የኒቨርሲቲው የህክምና መሳሪያዎች እና መድኃኒቶች ግዥዎችን ሲፈፅም በመመሪያ መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፣

ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 325,682.00 የተገዙት መድኃኒቶችና የህክምና እቃዎች በመድኃኒት የገቢ ደረሰኝ ገቢ መሆን ሲገባው ያለአግባብ በዕቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ገቢ እየተደረገ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

5. <u>ያለሂሳብ አርዕስቱ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው መመሪያው ይገልጻል:: መ/ቤቱ የወጪ ሂሳቦችን በትክክለኛው የሂሳብ አርዕስታቸው እየመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ የወጪ ሂሳቦች ናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

በድምሩ ብር 58,755,226.82 ከሂሳብ አርዕስቱ ውጪ በሌላ የሂሳብ አርዕስት የተመዘገበ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

6. <u>በጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ እቃው ተፈትሾ ጥራቱ ሳይረጋገጥ ገቢ የተረደገ እና ክፍያ የተፈጸመ የእቃን ግዥ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር9/2003 ንዑስ ቁጥር 22 ለ የመንግስት መስሪያ ቤቶች አዲስ ስቶክ ሲቀበሉ በሚከተሉት ላይ ተገቢዉን ማጣራት ማድረግ ይኖርባችዋል በሚለዉ ስር‹‹የእቃ ግምጃ ቤት ኃላፊዉ የእቃዉን ትክክለኛነት ከተሰጠዉ ትእዛዝ የእቃ ዝርዝር (specification] ጋርበማመሳከር ወይም ባለሞያ የሚፈልግ ከሆነም በባለሞያ ስለትክክለኘነቱ ማረጋገጫ ማግኘት እዳለባቸዉና በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 1 ቁጥር9.2 እና 9.4 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በሚለዉ ስር እቃዉ ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር መሰረት መቅረቡን ወይም አገልግሎት መሰጠቱንና አስፈላጊ ሲሆን እቃዉ ወይምአገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰራቱ ከሚመለከተዉ ባለሞያዎች የጽሁፍ ማረጋገጫ መቅረብ እዳለበት መመሪያዎቹ ቢያመለክቱም:-

አዲስ ምልምል ሰልጣኞች ተደራራቢ የብረት አልጋ ከትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ግዥ ለመፈጸም ዉል የገባ ቢሆንም ዕቃዎቹ

በታዘዙት ዓይነትና ጥራት ዝርዝር (Specification) መሰረት ለመቅረባቸው በዕቃ ጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ /Technical committee/ የተረጋገጠበት ማስረጃ ሳይቀርብ ተገዝተው ገቢ ለተደረጉ ዕቃዎች ግዥ ብር 21,976,983.00 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

7. <u>በወቅቱ ያልተወራረዱ ተሰብሳቢ፣</u>

በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፣ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለሥራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማሰረጃ ሲቀርብ ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችቶች እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ አለበት ይላል፡፡

ይሁን እንጅ የዩኒቨርሲቲው የሰኔ 30/2014 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 4211 ከተለያዩ ሰራተኞች በድምር ብር 15,123,161.73 ከሀምሌ 2014 ዓ/ም ጀምሮ የሚታይ ሲሆን በወቅቱ መሰብሰብ ሲገባው ያልተበሰበ የተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

8. <u>ስራ ላይ ያልዋለ በጀት፣</u>

የፌደራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12 ተራ ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛና የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በዚሁ መሰረት መሥሪያ ቤቱ በጀቱን የሚቆጣጠር መሆኑን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው ከ10% በላይ ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፣

ከመደበኛ በጀት በድምር ብር 10,399,308.72 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)፣

1. የቋሚ፣ አላቂ ዕቃዎች፣ የተማሪዎች ምግብ ቤት እና የመድሐኒት መደብር በተመለከተ፣

   የመሥሪያ ቤቱ የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 4 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ-መ) በተመለከተዉ መሰረት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ተሰብስበው ስልጣን በተሰጠው የመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

   1.1 ቢን ካርድ የተዘጋጀ ቢሆንም ንብረቶቹ ላይ ተያይዘው የማይቀመጡ መሆኑን፣

   1.2 በንብረት አስተዳደር ክፍል በ2014 ዓ.ም የሚወገዱ የቋሚና አላቂ ንብረቶች ዝርዝር፡-

   - የአናጺ እቃዎች በቁጥር ብዛት 11
   - የአላቂ አልባሳት በቁጥር ብዛት 20
   - የመመገቢያ እቃዎች በቁጥር ብዛት 24
   - የጽዳት እቃዎች በቁጥር ብዛት 2
   - የጽህፈት መሳሪያ በቁጥር ብዛት 79
   - የቋሚ ንብረት ተመላሽ ሆነው የሚወገዱ በቁጥር 31 የሚወገዱ እቃዎች ንብረት ክፍል ውስጥ የታየ መሆኑን፣

   1.3 በዩኒቨርስቲዉ የ2014 የቋሚና አላቂ ንብረት የቆጠራ ሪፖርት ተጠቃሎ ያልቀረበ
   መሆኑን፣

   1.4 የተማሪዎች ምግብ ማብስያ ውስጥና ዳቦ መጋገሪያ ክፍል ውስጥ፡-

   - ለረጅም ጊዜ ያለ አገልግሎት የቆመ የሥጋ ፍሪጅ የተገኘ መሆኑን፣
   - የፓስታ መቀቀያ ማሽን ያለአገልግሎት የተቀመጠ መሆኑን፣
   - የሻይ ማፍያ (ቡታ ጋዝ)ማሽን ሲልደር በግማሽ የሚሰራና የማይሰራ የተገኘ መሆኑን፣
   - ለረጅም ጊዜ የተቀመጠ የዳቦ መጋገርያ ማሽን እና የእቃ ማጠብያ ማሽን የተገኘ መሆኑን፣

- በዳቦ መጋገርያ ክፍል ዉስጥ አንድ የዳቦ መጋገርያ ማሽን ለረጅም ጊዜ ያላገልግሎት የተቀመጠ መሆኑን፣
- ሁለት የዳቦ ማኮፈሻያ ማሽን እና በግምት ከ15 በላይ የሚደርሱ የተበላሹና አገልግሎት የማይሰጡ ፓትራዎች የተገኘ መሆኑን፣
- የተማሪዎች የምግብ ማስቀመጭያ ስቶር ጠባብ መሆኑን፣

1.5 ዩኒቨርሲቲው መድሐኒት መደብር የመድሃኒት አቀማመጥና አያያዝ፣ የአገልግሎት

ዘመናቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች ሲታይ፡-

- ➢ Dispensary Pharmacy የነበሩ በቁጥር 77
- ➢ In pharmacy Store የነበሩ በቁጥር 80
- ➢ In injection room የነበሩ በቁጥር 4 በድምሩ 161 የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸው የሚወገዱ መድሃኒቶች መኖራቸውን፣ ተረጋግጧል፡፡

2. <u>የመስሪያ ቤቱን የውስጥ ቁጥጥር በተመለከተ፣</u>

በፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2008 ክፍል 3 አንቀጽ 10 ቁጥር 4 "የመ/ቤት የበላይ ኃላፊ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን ለመገምገምና የሚታዩ ችግሮችን፣ ሰነዶችንና ክፍተቶችን ለማረም የሚያስችል ግልጽ ዕቅድ ማዘጋጀት" አለበት ይላል፡፡ በተጨማሪ በዚሁ መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 14 ቁጥር 2 "በመስሪያ ቤቱ የስራ እንቅስቃሴ ወቅት ተለይተው የታወቁ ስጋቶችን ለማስቀረት ወይም የሚደርሱትን ጉዳት ለመቀነስ እንዲቻል እያንዳንዱ የመስሪያ ቤቱ የስራ ክፍል አንድን ስራ ለመፈጸም ሥራውን የሚያልፍበትን እያንዳንዱን ደረጃ በመዳሰስ ለስራው ተስማሚና ጠንካራ የውስጥ ቁጥር ስርዓት እንዲቀረጽ ማድረግ አለባቸው" ይላል፡፡ በዚህ መሰረት የዩንቨርሲቲው የ2014 በጀት አመት የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አደረጃጀትና አተገባበር በዳሰሳ ሂደት ሲታይ፡-

- ➢ ዩኒቨርሲቲው አመታዊ የግዥ እቅድ ያዘጋጀ ቢሆንም የተለያዩ ግዥዎችከግዥ እቅድ ውጭ የተገዙ መሆናቸው፣ ለምሳሌ የደንብ ልብስ ግዥ፣

➢ አብዛኞቹ የወጪ ሂሳቦች ገንዘብና ኢኮኖሚ ባዘጋጀው ትክክለኛ የሂሳብ መደብ አወቃቀር መሰረት ያልተመዘገቡ መሆኑን፣

➢ ዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ያሉ ህንጻዎች ያልተመዘገቡና ምን ያህል ህንጻዎች እንዳሉ ሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ የሌለ መሆኑን፣

➢ ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ምልምል ሰልጣኞችን ከየቦታው መልምሎ የሚያሰለጥን ቢሆንም መልማዮች ወደ ቦታው ሄደው ሲመለሱና አበል ሲወራረድ ግልጽ የሆነ ማስረጃ አለመቅረቡ ለምሳሌ የሰልጣኞች ፊርማ ማስረጃ ላይ የአንድ ሰው ፊርማ ከተለያዩ ስሞች ላይ ተደጋጋሚ ተፈርሞ በመገኘቱ ለሰልጣኞች መድረሱ አጠራጣሪ መሆኑ፣ውሎ አበል ተከፈላቸው ተብሎ አበል የሚወራረድላቸው ሰልጣኞች ከክልልና ከዞን ተመልምለው ሲጨርሱ ክልሉ ወይም ዞኑ በቁጥር ስንት ሰልጣኝ ወደ ስልጠና ቦታ እንደላከና ማሰልጠኛ ቦታ ላይ ሲደርሱ ስንት ምልምሎች በትክክል ቦታው ላይ እንደደረሱ የሚገልጽ ማስረጃ ማረጋገጫ የማይያዝ መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡

3. <u>የውስጥ ኦዲት በተመለከተ፣</u>

የፌደራል መንግስት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 ክፍል አምስት የውሰጥ ኦዲት ዕቅድና ሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳ ላይ በንኡስ አንቀፅ 3 በኦዲት ዕቅዱ መሠረት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት እስከ ጥቅምት 30፤ የሁለተኛ ሩብ ዓመት እስከ ጥር 30፣ የሶስተኛ ሩብ ዓመት እስከ ሚያዚያ 30 ድረስ እና የአራተኛ ሩብ ዓመት እስከ ነሐሴ 15 መሆን እንዳለበት ይገልፃል፡፡

በዚሁ በጊዜ ሰሌዳ መሠረት የ2014 በጀት ዓመት የውስጥ ኦዲት ሥራ መከናወኑን /መሠራቱን/ በምናጣራበት ጊዜ ወቅቱን ጠብቆ ከአንደኛ ሩብ ዓመት እስከ አራተኛ ሩብ ዓመት ድረስ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ያልቀረበ መሆኑን እና እስከ ጥቅምት 30/2014 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ብቻ ለሚመለከታው አካል ቀርቦ ምላሽ ያገኘ መሆኑን እና በተጨማሪም የውስጥ ኦዲት በሰው ኃይል ያልተሟላና በከፊል ያለውም የሰው ኃይል በኦዲት ሥራ ልምድ የሌለው መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

የህግ ጉዳዮች በተመለከተ (Compliance Issue)፣

1. ያለሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ደረሰኝ የተፈፀመ ግዥ

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 19 እና 20 እንዲሁም በታክስ ደረሰኝ አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011 አንቀጽ 9 በተገለጸው መሰረት መሰረት ማንኛውም በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የመጠቀም ግዴታ ያለበት ተቋም የሽያጭ መሳሪያው በጥገና ላይ ባለበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ከታተመ ደረሰኝ ውጭ በሌላ ማናቸውም ዓይነት ደረሰኝ ማከናወን እንደማይችል ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት መ/ቤቱ ለሚፈፅመው ክፍያ ተገቢውን ደረሰኝ የሚቀበል መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

በድምር ብር 24,918,946.90 በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የታተመ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

2. ከተሽርካሪ ኪራይ አገልግሎት ግዥ ያልተቀነሰ ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ፣

የፌዴራል መንግሥት የቅድመ ታክስ ሥርዓትን አስተደደር አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 3.4 ንዕስ አንቀፅ 3.4.1 ከተከፋይ ሂሣቦች ላይ ግብር ተቀናሽ የሚደረግባቸው የዕቃና የአገልግሎት ግዥ ዝርዝር ተራ ቁ 1 እና 2 እንዲሁም በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 24 ተራ ቁጥር 1እና2 መሠረት ግዥ ፈጻሚ አካል የዕቃና የአገልግሎት ግዥ በአንድ ጊዜ ከብር 10,000.00 በላይ ግዥ እና ከብር 500.00 በላይ የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም ከተከፋይ ሂሳብ ላይ መቀነስ የሚገባው ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ 2% እየተቀነሰ ገቢ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

ዩኒቨርሲቲው ለተሽርካሪ አገልግሎት ግዥ ክፍያ ሲፈፀም ለባለጥቅሙ ከሚከፈለው ሂሳብ ላይ መቀነስ የነበረበት 2% የቅድመ ክፍያ ታክስ (ዊዝ ሆልዲንግ ታክስ) ብር 136,848.51 ሳይቀነስ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3. በዱቤ የሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደ ሂሳብ፣

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች ንዑስ ቁጥር 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚገባ ሲወራረድ

በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦሪጂናል ደረሰኝ መሆን እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡

ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ለተለያየ የአገልግሎቶች እና የዕቃ ግዥ ሲፈጽም የእጅ በእጅ የሽያጭ ደረሰኝ በመቀበል ሂሳቡ መወራረድ ሲገባው በዱቤ የሽያጭ ደረሰኝ በድምሩ ብር 1,828,072.48 ተወራርዶ የተገኘ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

4. <u>ከተፈቀደው በላይ ስራ ላይ የዋለ በጀት፣</u>

በፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት ዩኒቨርሲቲው በጀቱን የሚቆጣጠር መሆኑን ኦዲት ሲደረግ፣

ከመደበኛ በጀት በድምር ብር 4,098,914.87 ሳይፈቀድ በማዛወር ከተደለደለው በጀት በላይ የተጠቀመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

5. <u>በወቅቱ ለገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ያልተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ (የተከፋይ ሂሳብ፣)</u>

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ ሀ ማናቸውም ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብ መያዝ እንዳለበት እንዲሁም አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5/ሐ የተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን የግብር እና ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው ግብር አስገቢ አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ እንዳለበት ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው የሰኔ 30/2014 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 5059 ብር 12,074,117.32 ከሀምሌ 2014 ዓ/ም ጀምሮ የሚታይ ሲሆን በወቅቱ ለገቢዎችና ጉምሩክ መከፈል ሲገባው ያልተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ ሂሳብ ስለመኖሩ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት